# ኢንቨስትመንት ዛሬ

**ደስታ ኃይሉ 10-04-17**

በአሁኑ ወቅት የአገራችን የኢንቨስትመንት በተሻለ ደረጃ ላይ ይገኛል። የዘርፉን አፈፃፀም ተስፋ ሰጪ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትንም በተገቢው መንገድ በማሳብ ላይ ይገኛል። ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የአገር ወስጥና የውጭ ባለሃብቶች ዘርፉን ለማስደግ ከፍተኛ ጥረት በሚድረግ ላይ ይገኛሉ።

ባለፉት ጊዜያት የሀገራችንን ምቹ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ተጠቅመው መዋዕለ ንዋያቸውን በማፍሰስ ላይ የሚገኙት የቻይና፣ የቱርክ፣ የህንድ፣ የአወሮፓ፣ የአረብ ሀገሮች ትልልቅ ኩባንያዎችና ባለ ሀብቶች ከመኖራቸው ባሻገር፤ እንደነ ሳምሰንግ፣ በጂኦተርማል ሃይድሮ ፓወር ፕሮጀክት ላይ ለማሰማራት በዝግጅት ላይ የሚገኘው ግዙፉ የአሜሪካ ኩባንያ፣ በሚድን ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩት የካናዳና የአወስትራሊያ ኩባንያዎችና ሌሎች ፍላጎት ያላቸው ኢንቨስተሮች በማብራከታቸው አሳማኝ አስረጅ በመሆናቸው ነው።

ለኢንቨስትመንት ፍሰት ሰንሰለት ዋነኛው ምክንያት የኢፊዲሪ መንግስት በሀገራችን የተፋጠነ ልማት ለማምጣት የሚያስችል ትክክለኛ ፖሊሲና ስትራቴጂ ከመንደፉም ባሻገር፤ በተግባር መተርጎም መቻሉም ይመስለኛል፡፡ እርግጥ በሀገራችን እየተመዘገበ ለሚገኘው ለወጥ በዋናነት ሊጠቀስ የሚችለው ጉዳይ የጠራ ማስመር የያዘ፣ ሀገራዊውን ወቅታዊና ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ በተግባር ላይ የሚያወል አመራርና በህዝባዊ ተሳትፎ የተደገፈ አቅጣጫ የሚከተል የልማታዊ መንግስት መኖሩ የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይመስለኝም፡፡

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ መንግስት በሀገሪቱ መዋዕለ ንዋያቸውን በማፍሰስ፣ በኢንቨስትመንት ለማሰማራት ፍላጎት ያላቸው የውጭ ባለሀብቶችን ለማሳብ የተለያዩ ማበረታቻዎችን በማመቻቸት በሩን ከፍት በሚድረግና በተለያዩ አለም አቀፋዊ መድረኮች ተጨባጭ ሁኔታውን በማስረዳት በርካታ ባለሃብቶችን በማሳብ ላይ ነው፡፡

ዛሬ ላይ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ማስኮች በተለይም በግብርና፣ በማኑፋክቸሪንግና ኢንዱስትሪ ዘርፎች የተሰማሩ የውጭ ባለሀብቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ ማምጣት ችሏል፡፡ ሀገሪቱ ለኢንቨስትመንት ምቹ መሆኗን የተገነዘቡ በርካታ የውጭ ኩባንያዎችና ባለሃብቶች መዋዕለ ንዋያቸውን ለማፍሰስ ከፍተኛ ፍላጎት የማሳየታቸው ምስጢርም ይኸው ይመስለኛል።

አገራችን በምትከተለው ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ትክክለኛ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ በግሉ ባለሃብት ማሰራት የሚገባቸውና በመንግስት ሊከናወኑ የሚገቡ ተግባራት ተለይተው በማካሄዳቸው በሁለቱም በኩል ወጤቶች እየተመዘገቡ ነው። የሀገር ወስጥም ይሁን የውጭ ባለሃብቶችን የሚሰማሩባቸውን ዘርፎች በማለየት አንፃራዊ በመሆነ መንገድ ለሀገሪቱ ዕድገት የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ተደርጓል።

የግሉ ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገቱ አንቀሳቃሽ ሞተር ሚሆኑ በመንግሥት ታምኖበት በፍትሃዊ ወድድር ላይ እንዲመሰረት በመደረጉ ባለፉት 26 ዓመታት በርካታ ሐገራዊ ባለሃብቶች ተፈጥረዋል፡፡ እነአዚህ ባለሃብቶች በዓለም የገበያ ወድድር ወስጥ ጠንካራ አቅም እንዲኖራቸው ቀጣይነት ያላቸው ድጋፎች እየተደረገላቸው ነው።

በእነዚህ ዓመታት ወስጥ ባለሃብቶቹ የሃብት ባለቤት እንዲሆኑና ለዜጎች የስራ ዕድል እንዲፈጥሩ ሁኔታዎች ተመቻችተወላቸው በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ አሻራቸወን ማኖረፍ ችለዋል። ብዙዎቹ ሀብት እንዲያፈሩ እና ለብዙ ዜጎች የስራ እድል እንዲፈጥሩ ከማስቻሉም በላይ በኢኮኖሚው ወስጥ የራሳቸወን አሻራ ማኖረፍ ችለዋል።

የሀገር ወስጥን ባለሃብቶች ከውጭ ባለሃብቶች ጋር በማቀናጀት ለመፍጠር የተቻለው የገበያ ትስስርም ምቹ የኢንቨስትመንት ማሰረትን ጥሏል ማለት ይቻላል። ከእነዚህ ወስጥ የወጪ ንግድ የብድር ዋስትና ሥርዓት መተግበር፣ የወጪ ምንዛሪ ተመን ማስተካከልና የምንዛሪ ዋጋው በገበያ እንዲወሰን ማድረግ በዋነኛነት የሚጠቀሱ ምቹ ሁኔታዎች ናቸው።

የኤክስፖርት ምርትን ከቀረጥ ነፃ ማድረግ፣ ለኢንቨስትመንት ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ የካፒታል ዕቃዎችና ግብዓቶች ያለ ቅድሙ ሁኔታ የሚገበብትን ዕድል የመፍጠር ብሎም ባለሃብቶቹ ለስራቸው የሚሆን መሬት በሊዝ እንዲያገኙ መደረጉ ተጨማሪ አመቺ መደላድሎች ነበሩ። እነዚህ በመንግስት በኩል አቨስትመንትን ለማበረታታት የተወሰዱ እርምጃዎች የቅጭ ባለሃብቶች ሀገራችን ላይ ዓይናቸወን እንዲጥሉ ያደረጉ ተግባራት ናቸው።

እዚህ ላይ አንድ ዕወነታን ማንሳት አግባብነት ያለው ይመስለኛል። ይኸወም ሀገራችን የትምህርት፣ የጤና፣ የመንገድና የንፁህ ማጠጥ ወሃ ማሰረተ–ልማቶች ሙሉ ለሙሉ ያልተሟሉባት በመሆኗ ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ ከሀገራዊው ዕድገት ጋር የሚመጣጠን ግንባታዎች ለማካሄድ በመንግስት በኩል እንደሚካሄደው በተመሳሳይ ሁኔታ የግሉ ባለሃብት ሊከናወን አለመቻሉ ነው። የግሉ ዘርፍ የአኮኖሚ ዕድገቱ አንቀሳቃሽ ሞተር ሚሆኑ በመንግሥት ታምኖበት በፍትሃዊ ወድድር ላይ እንዲመሰረት በመደረጉ ባለፉት ዓመታት በርካታ ሃገራዊ ባለሃብቶች እንዲፈጠሩ ቢደረግም፤ ባለሃብቱ ሊሰማራባቸው በሚይችላቸው ዘርፎች መንግስት በተሚጠ አኳኋን ጣልቃ ገብቶ ልማቱን በዋነኝነት በማንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

እነዚህ ድምር ወጤቶች የሀገራችን መፃዒ ዕድል አመላካች ይመስሉኛል። መንግስት የሚከተለው የኢንቨስትመንት ፖሊሲ የሀገር ወስጥ ባለሃብቶችን ያሳደገና የስራ ዕድል የፈጠረ ብቻ አይደለም። ይልቁንም የሀገራችንን የወጭ ምንዛሬ እጥረት ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት እንደ የሀገር ወስጥ ባለሃብቶች ሁሉ ተመጣጣኝ የወጭ ምንዛሬ ግኝት ማምጣት የሚችሉ የወጭ ባለሃብቶችም ወደ ሀገራችን እንዲተሙ አድርጓቸዋል።

ታዲያ ይህ በጎ የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዳይደናቀፍ በመንግስት ፈፃሚዎች በኩል ብርቱ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል። በተለያዩ ወቅቶች የውጭ ባለሃብቶች የሚያሰሙትና ሆን ተብሎ በአስፈፃሚዎች የሚፈፀም የሚመስሉ አላስፈላጊ ውጣ ውረዶችን ማስቀረት ይገባል።

ከዚህ ጎን ለጎንም በኢንቬስትመንት ስም ወደ ሀገር ወስጥ ገብተው ምንም ዓይነት እሴት ሚጨምር ያልቻሉ ባላሀብቶችን ሚዛኑን በጠበቀና ፍሰቱን በሚያስተጓጉል ሚልኩ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል።

መንግስት ለሀገራችን ኢንቨስተሮች ሙሉ ዋስተና ይሰጣል። ማንኛውም ባለሃብት እዚህ ሀገር ወስጭ ለሚያፈሰው መዋእለ ነዋይ መንግስት ኃላፊነት ወስዶ የሚሰራ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ይህ ሁኔታም በሀገራችን ወስጥ የተጀመረው የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዳይስተጓጎል አድርጎታል።

ይህ የመንግሥት ተግባር እንዲጠናከርና በተለይም የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ወደ አገራችን እንዲገባ ሁሉም የድርሻውን መወጣት አለበት። ኢንቨስትመንት ለዜጎች ስራን የሚፈጥርና ገቢያቸውም በዚያው ልክ እንዲሻሻል ያደርጋል። ገቢው የተሻሻለ ዜጋም የህይወት ዘይቤውን በማሻወጥ ሌሎች የደረሱበት ደረጃ ይደርሳል።